# ኢትኦጵ

ቅፅ 2 ቁጥር 024 ግንቦት 1993 ዓ.ም



## «ከእንግዲህ ሕወሓትን ማስተካከል አይቻልም»



## ግደይ ዘርዓፅዮን

(የቀድሞ የሕወሐት ም/ሊቀመንበር)



## ከግንቦት እስከ ግንቦት




# «እነ አቶ ስዬ የቤት-መንግሥቱን አንጃ እያቀጣጠሉ ነው ያሉት»

ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

**ኢትዮጵ:- ካለፈው ቃለ ምልልስ ወዲህ በሃገራችን ብዙ ሂደቶች ተከናውኗል:: በሕወሐት ውስጥ የተፈጠረው ቀውስ እንዴት ይመለከቱታል? ቀጣዩን ቃለምልልስ በዚህ ብንጀምር::**

<u>ዶ/ር ነገደ:-</u> በዚህ ጥያቄም ሆነ በወጣቶቹ ንቅናቄ መልስ ለመስጠት የምሞክረው ባለፈው እትማችሁ ስለብሔር ጥያቄና ስለብሔር ድርጅቶች፣ ስለህዝባችን ትግልና ስለዚህ ትግል የቅንብር ችግር፣ ስለባዕዳን ሚናና ስለማሕበራዊ ፍትሕ ቀውስ ካነሳኋቸው ነጥቦች እየተነሳሁ ነው:: በሕወሐት ውስጥ የተከሰተው ቀውስ አንድን ብሔር በውስጡ ምንም አይነት ቅራኔ እንደሌለበት፣ ዝግ ስብስብ አድርጐ የሚያቀርበው የሁለቱም አንጃዎች አጥፊ ቲዎሪ ምን ያህል የተሳሳተና ምን ያህል በ«ሳይንሱም በመጽሀፉም» የሌለ ቲዎሪ እንደሆነ በግልፅ ያሳየ ይመስለኛል:: መኢሶን ከጥንቱም ቢሆን የሚለው የኢትዮጵያ ዲሞክራቶች በብሔሮች መብትና በሃገራችን አንድነት ጥያቄ የማያሻማ ዲሞክራሲያዊ አቋም ይዘው በዚህ ላይ እንደ ፖለቲካ አቋማቸው እንደ ርዕዮተ አለማቸው፣ እንደ ማሕበራዊ ፕሮጌያቸው ቀኝ፣ ግራ፣ መሃል፣ ሊበራል፣ በሳል ዲሞክራት፣ ሶሻሊስት እያሉ በሃገር አቀፍና በሕብረብሄር ደረጃ ተደራጅተው መታገላቸው ብቻ ነው ይቺን አገራችንን ወደ ኖርማልነት የሚያመጣት ጤናማ ሂደት የሚል ጽኑ አቋም አለው:: ሁሉም ለብሔሩ፣ ሁሉም ለየብሔሩ የሚለውና ባለፈው ቃለምልልስ የተቻለኝን ያህል ሳጋልጠው የሞከርኩት የሁለቱ አንጃዎች ያራምዱት የነበረው አጉል ቲዎሪ ዛሬ ክስረቱ እየተጋለጠ ይመስለኛል:: ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የግለሰብና ሌሎች መሠረታዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንደዚሁም የሕግ የበላይነት በተረጋገጠባት አገራችን ሁሉም የብሔርንና የክልልን አጥር ሰባብሮ ክፍ ብዬ በጠቀስኩት መልክ በአገር አቀፍ ደረጃ መሸጋሸግ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን አይቀሬ እየሆነ ይመጣል ባይ ነኝ:: ከዚህ የወያኔዎች ውስጣዊ ቀውስ ለኢትዮጵያችን በጎ ነገር ሊመጣ የሚችለው ግጭታቸው ይኼን ሂደት በሚያግዝ ሁኔታ የተፈታ እንደሆነ ብቻ ነው:: የሃገሪቱ ዲሞክራቶች ደግሞ መስራት ያለባቸው ቀውሱ በዚህ መልክ እንዲፈታ የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ነው::

ከዚህ በፊት እንዳልኩት ባለፉት አስር አመታት ቀስ በቀስ በወያኔዎች የማያወላዳ የበላይነት ሕብረብሔር የሆነ አንድ ፀረ-ዲሞክራቲክ አፋኝና ግፈኛ ስርዓት በአገር አቀፍ ደረጃ እየተገነባ ነው:: አሁን የተከሰተው ውጥረት ቢያንስ በነ አቶ መለስ አንጃ በኩል ሌላ ውጤት አይኖረውም:: ከዚህና የወጣቱ ትግል ከፈጠረባቸው ውጥረት ለመውጣት እንደጀመሩት በለየለት የጭፍጨፋና የጭካኔ ሂደት ሊቀጥሉ ይችላሉ:: ይኸንን ጊዜ ያሳየዋል:: ጊዜ ሳይጠበቅ ካሁኑ መባል የሚቻል ነገር ግን አለ:: ከእንግዲህ በሚመጣው የኃይል አሰላለፍ አፍ ሞልቶ ማን በማን ላይ እንደሚለጠፍ መናገር ባይቻልም የኢሕአዴግ ሕብረ ብሄራዊ ገጽታ እየጉላ የሚሄድበት ሁኔታ አለ:: የእነ አቶ ስዬም አንጃ ቢሆን ቅያሬ ስትራቴጂ ሊኖረው አይችልም:: ከላይ ሻዕቢያን ያህል «ደመኛ» ጠላት አለው:: በአለም አቀፍ ደረጃ ምእራባውያን በአንጃዎቹ ግጭት አላስፈላጊና አደገኛ ወገናዊ አቋም መርጠው በየት እንዳመጡት ባናውቅም እነ አቶ መለስን «ዲሞክራት» እያሉ እያሞካሹ ናቸው:: የኢአዴግ አባል ድርጅቶች አቋማቸውን ግልጽ አድርገዋል:: የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰዎች ካለፈው አክራሪ የትግራይ ብሔረተኛነትም ሆነ ከወያኔ አፋኝ አሠራር ምን ያህል ራሳቸውን እንደነጠሉ ግልጽ ላልሆነለት በጎሪጥ እያያቸው ይገኛል:: በትግራይና በውጭ አገር ያሉ የትግራይ ተወላጆች አካባቢ እንኳን ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው ብንል በጎረቤትና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተ በጀባቸው ያለውን አልያንስ ብቻቸውን ሊቋቋሙበት የሚችሉበት ምንም ተአምር አይኖርም:: ባጭሩ አድማሳቸውን ከትግራይ ክልልና ከትግራይ ብሔር አስፍተው፣ ቁልፍ በሆኑት የኢትዮጵያ ችግሮች ላይ አቋማቸውን ግልጽ አድርገው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር እነሱም እንደ ኢሕአዴግ ወደ ሕብረ-ብሔርነት መሄድ አለባቸው:: ቅያሪ ስትራቴጂ ሊኖራቸው አይችልም የምለው ለዚህ ነው::



**ኢትዮጵ:- ይኸ ሲባል ተቃዋሚ ኃይሎች በዚህ ቀውስ ውስጥ ወገን ለይተው መቆም አለባቸው ማለት ነው? ከወገኑስ ከየትኛው አንጃ?**

<u>ዶ/ር ነገደ:-</u> በፍጹም:: አሁን ባለንበት ደረጃ ተቃዋሚዎች እነ አቶ መለስንም ሆነ እነ አቶ ስዬን ደግፈው መውጣት የለባቸውም:: በአጠቃላይ በሃገሪቱ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች ራሳቸውን መጠየቅ ያለባቸው ከአንጃዎቹ አንጻር ምን አቋም እንያዝ የሚለውን ጥያቄ አይደለም:: አንጃዎቹ ናቸው ከኛ ከተቃዋሚዎችና በአጠቃላይ ከሕዝባችን ጥያቄዎች አንጻር አቋም መያዝ ያለባቸው:: ይህ ጉዳይ በደንብ መስመር ያለበት ጉዳይ ይመስለኛል:: ሁለቱ አንጃዎች ለአስር ዓመት ረግጠው የያዟቸው የሕዝባችን መብቶች ጥያቄዎች አሉ፤ የፀረ ዲሞክራሲ፣ የአፈናና የዘፈቀደ አገዛዛቸው ማክተም ጥያቄ አለ፤ ውሸታቸውን እንወክለዋለን በሚሉት በትግራይ ሕዝብ ስም የጫኑብን ሕዝብን ከሕዝብ የሚያናክሰው ፖሊሲያቸው ጥያቄ አለ፤ የጫኑብን ግፈኛና በሙሰኛነት የተበከለ የዘረፋና የስድ ገበያ ኢኮኖሚ ስርአት አለ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ አገራችንን ከአይቀሬውና ከአስከፊው ትርምስ አትርፈን በጐ የዲሞክራሲያዊ ሽግግር ጐዳና ለማስያዝ በኢትፖድህ ብቻ ሳይሆን ከሱ ውጭ ባሉ ተቃዋሚዎችና በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ የቀረበው ዛሬ ገደሉ አፋፍ ላይ በመሆናችን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አንገብጋቢ የሆነው የሁሉን አቀፍ ጉባኤና የብሔራዊ እርቅ ጥያቄ አለ:: አንጃዎቹን መመዘን ያለብን ከነዚህ ➔

ቁልፍ ጥያቄዎች አንጻር ነው፡፡

ሁለተኛ ደግሞ በነዚህ ቁልፍ ጥያቄዎች ላይ አንጃዎቹ በሕዝብ ፊት ግልጽ አቋም ይዘው ባይወጡ በዚያው በውስጥ ትግል አንዱ ሌላውን አሸንፎ ቢወጣ ለሃገራችን ይበልጥ ችግር እንጂ ምንም በጐ ነገር ስለማይመጣ ወገናዊ አቋም የምንይዝበት ምንም ምክንያት አይታየኝም፡፡ በዚህ ጉዳይ ብዙ አስገራሚ ነገሮች እያየን ነው፡፡ ይሽጋሸጉ፣ ግልጽ አቋም ይያዙ ማለትን ትቶ አንዳንዱ ይኸኛው ቢያሸንፍ ይሻላል ወይም ያኛው ቢያሸንፍ ይመረጣል እያለ መተቸት ይዟል፡፡ በዚህ ጉዳይ አንድ ምሁር የነ አቶ መለስ ወገን ቢያሸንፍ የተገደበ ዲሞክራሲ፣ የተገደበ ካፒታሊዝም ያበቃለታል በማለት ሲያንቀላልጩን በአንድ ጋዜጣ አንብቤያለሁ፡፡ እኒህ ምሁር በምን ጥበብ ሁለቱን አቀራኝተው ማራመድ እንደቻሉ ግልጽ አይደለም፡፡ ያልተገደበ ካፒታሊዝም ከተባለ እኮ በብዙዎች ላይ የሚያወርደውን ጥፋት ለመቃወም የሚንቀሳቀሱትን ኃይሎች ለመቋቋም ሲባል ዲሞክራሲን ከመገደብም አልፎ ወደፋሺዝም ሊሄድ ይችላል፡፡ ያልተገደበ ዲሞክራሲ ከተባለ ደግሞ የግድ ካፒታሊዝም ስነ ስርአት እንዲይዝ ይገደዳል፡፡ በዲሞክራሲ ያልተገደበና ስነ ስርአት ያልያዘ ካፒታሊዝም የ19ኛው ክፍለ ዘመን ካፒታሊዝም ነበር፡፡ ይኸ ሌላ ክርክር ነው፤ ብዙም አልገባበት ለጊዜው፡፡ ከምሁሩ አባባል አንድ ያስገረመኝ ነገር አለ፡፡ የነ አቶ መለስ ወገን በአሸናፊነት ቢወጣ ለሃገሪቱ አንድ የወደፊት እርምጃ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ባለፈው ቃለምልልስ ላይ ለመጠቆም እንደሞከርኩት እነ አቶ መለስ በሃገራችን በመትከል ላይ ያሉት ግፈኛ ስርአት ሕዝባችንን ዲሁማናይዝ እያደረገ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶችን ቀቢፀ ተስፋ ያደረገ፣ የሕብረተሰባችንን ሞራል፣ እሴት፣ ስነልቦና በየቀኑ እየተፈታተነ የሃገራችንን ሕልውና ከእለት እለት ጥያቄ ውስጥ እያስገባ የሚሄድ ስርአት ነው፡፡ በዚህ መልክ አገራችን የጥፋት አፋፍ ላይ ቆማ እያለች የምሁሩ «ወደፊት» ርምጃ ገደል ለመግባት እንጂ ለኔ ሌላ ትርጉም አይሰጠኝም፡፡ የነ አቶ ስዬም አሸናፊነት ጉዳይ አልሸሹም ዘወር አሉ ነው፡፡ አሁን በያዙት አቋም የነ አቶ መለስን «ቡርዥዋ ዲሞክራሲ» ነቅፈው ስለ ወዛደሩና ስለ ገበሬው ዲሞክራሲ እናውራችሁ ቢሉን ውጤቱ አነሰ ቢሉት ተቀነሰ እንደሚባለው እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡

**ሲትሶጵ፡-** ግን እኮ በሁለቱ ወገኖች መሃከል ሕዝቡ እየተቸባቸው ያሉ የፖለቲካ አቋም ልዩነቶች አሉ፡፡ ምን አይነት ዲሞክራሲ? ከባዕዳን ኃያላን ጋር ምን አይነት ግንኙነት? የምንከተለው የኢኮኖሚ ስርአት ምን መሆን አለበት? ተቃዋሚዎችም ሆነ ሕዝቡ ከነዚህ ጥያቄዎች አንጻር መተቸትና አቋም መያዝ የለባቸውም?

ዶ/ር ነገደ፡- ብዙዎች እየተቹና አቋም እየያዙ ናቸው፡፡ በኔ ግምት አሁን ባለንበት ደረጃ ይህንን ቀውስ ለመፍታት ለእነሱም፣ ለእኛም ለሃገራችንም በጎ የሚሆነውን አካሄድ በሌላ በኩል ደግሞ ጥፋት የሚያመጣውን ጎዳና ማጋለጥ ይበልጥ ቁም ነገር አለው ባይ ነኝ፡፡ በተያዘው አካሄድ ማለትም በውስጥ ሽኩቻና አሁን በአቶ ክንፈ መገደል ከተከፈተው ነባሩ የፖለቲካ ልዩነት «መፍቻ» ዘዴ እንውጣ ማለት መቻል አለብን፡፡ «ይባባሉና ይለይላቸው» የሚሉ ሰዎች አጋጥመውኛል፡- ይዳከማሉ ከሚል አጉል ስሜት፡፡ ይኸ የዋሁ ሰውዬ «የቤቱ መቃጠል ለትኋኑ» በጀኝ ያለውን ነው የሚያስታውሰኝ፡፡ በዚህ በመመታታት ሂደት ማንም ይሁን ማን በአሸናፊነት ቢወጣ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ያሸነፍኩ ባይ ወገን ይበልጥ አፋኝ ሆኖ እንጂ ይበልጥ ዲሞክራሲያዊ ሆኖ አይወጣም፡፡ በእንደዚህ አይነቱ ጉዳይ እኛ መኢሶኖች ተጨባጭ ልምድ አለን፡፡ በ1969 ዓ.ም የነኮሎኔል መንግስቱና የነ መቶ አለቃ አለማየሁ አንጃዎች በሚተራመሱበት ወቅት አቋማችን አንዱ አንዱን በኃይል እንዳያስወግድ መሞከር ነበር፡፡ በውስጥ ሽኩቻ አንዱ አንዱን አሸንፎ ከወጣ አሸነፍኩ ባይ አደገኛ ኃይል ይሆናል በሚል ትክክለኛ ስሌት፡፡ ኮሎኔሉ ማንንም ሳያማክሩ እርምጃ ወሰዱ፡፡ እኛ ነገሩ ካለቀ በኋላ በስልክ ነው በየቤታችን የተነገረን፡- «ሰዎቹ ላይ እርምጃ ተወስዷል» የሚል፡፡ ከዚያ በኋላ የመጣውን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ... ቀይ ሽብር... ወዘተ እናውቀዋለን፡፡

ለዚህ ነው ስለአዲስ የልዩነት መፍቻ ዘዴ ባሕል ብዙ ማውራት የምፈልገው፡፡ ለዚህ ነው ተጋግዘን በሃገራችን የተረጋጋ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ እንፍጠር፣ ልዩነቶችም በዚህ ክልልና መድረክ ይፈቱ ማለት ያለብን፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ ተግባራችን ይኸኛው ወገን ልክ ነው... ያኛው አንጃ ይሻላል ማለት ሳይሆን ስለዲሞክራሲ መጨቃጨቅ ያለብን፡፡ ለዚህ ነው ለምሳሌ የኢተፖድህ መግለጫ 1ኛ/ የነ አቶ መለስ አንጃ ለጊዜው ባገኘው የበላይነትና በሚቆጣጠረው የመንግስት መዋቅር ተጠቅሞ በነ አቶ ስዬ አንጃ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ምንም አይነት የኃይልና ሕገወጥ እርምጃ እንዳይወስድ፣ 2ኛ/ የነ አቶ ስዬ አንጃ ያሻውን አቋም እንደያዘ በትግራይም ሆነ በመላ ሃገሪቱ የመደራጀትና የመንቀሳቀስ መብቱ እንዲከበርለት የጠየቅነው፡፡

ይህ አቋማችን ከነ አቶ ስዬ አቋም የመስማማት ወይም ያለመስማማት ጥያቄ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት አንድ ፈረንሳዊ ዲሞክራት በትክክል እንዳስቀመጠው መሆኑ ነው፡፡ «በምትለው አልስማማም፤ ግን የምትለውን የማለት መብትህ እንዲከበር ካስፈለገ ሕይወቴን ለመሰዋት ዝግጁ ነኝ» የኛም ምሁራን፣ የኛም የፖለቲካ ሰዎች 21ኛው ክፍለ ዘመን እየገባን ባለንበት ወቅት እዚች ቀላልና ዲሞክራቲክ እይታ መድረስ አለባቸው እላለሁ፡፡ ይህንን ሳያደርጉ፣ ለዚህ መብት ሳይሟገቱ የነ አቶ ስዬን አቋም በሆነ ባልሆነው መተቸት ሊከተል የሚችለውን አደጋ ሳያጤኑ እነ አቶ መለስን አይዟችሁ ከማለት ሌላ ትርጉም የለውም፡፡

**ሲትሶጵ፡- ይህንን እያስመረሩ ለዲሞክራሲ መስፈን እየታገሉ በደፉ ሁለቱ የሚያንጸባርቁትን አቋም መተቸት አይቻልም?**

ዶ/ር ነገደ፡- ከፍ ብዬ እንዳልኩት የአቀም መውሰድ ነገር ከመጣ ዋናው ቁም ነገር አንጃዎቹ ሕዝባቸንንና ተቃዋሚ ኃይሎች ከሚያቀርቧቸው በተለይም ደግሞ የብሔራዊ ውይይትና የሁሉን አቀፍ ጉባኤ አንጻር አቀም መውሰድ ይጠበቅባቸዋል የሚለው አስተሳሰብ እንደተጠበቀ ሆኖና ችግሩ በዲሞክራሲ ይፈታ የሚለውን ጥያቄ አስረግጦ እስከአሁን ድረስ ስለተንጸባረቁት ልዩነቶች ከመተቸት የሚያግድ ነገር የለም፡፡

አሉ የሚባሉት ዋና ዋና ልዩነቶች ምንድን ናቸው? አንዳንዶች ልዩነቶች እነ አቶ ስዬ አድማሳቸውን ከሕወሐት፣ ከትግራይ ብሔርና ከትግራይ ክልል እንዳላሰፉ፣ ሌሎቹ ራዕያቸውን ከኛም አገር ከዓለም አቀፉም ሁኔታ ውጪ ትምህርት ቀስመው ያላሻሻሉ መሆናቸውን የሚያንጸባርቁ ልዩነቶች ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ በኔ ግምት መሠረታዊ ሊባሉ የሚችሉ ነጥቦች ናቸው፡፡

ከአድማስ መጥበብ የምፈርጃቸው የልዩነት ነጥቦች እነ አቶ ስዬ «የቤተመንግስቱ አንጃ» በሕወሃት ውስጥ ደንብ ጣሰ፣ ዲሞክራሲን አላከበረም፣ የሕግ የበላይነትን ረገጠ እያሉ የሚደረድሩአቸው ውንጀላዎች ናቸው፡፡ አስር ዓመት ሙሉ በአንድነት ሆነው በሃገራችን ላይ የጫኑትን አፋኝ ስርዓት ዘወርወር ብለው መቃኘት እንዳልቻሉ ግልጽ ነው፡፡ በፓሪሱ የኢተፖድህ መግለጫ ላይ ይህን በግልጽ ያስቀመጥነው ጉዳይ ነው፡፡ በአንድ አገር ላይ በአንድ ብሔር ወይም ድርጅት ስም አፋኝ ስርአት ሲተከል በዚያ ብሔር ወይም ድርጅት ውስጥ ዲሞክራሲ ይኖራል ማለት ዘበት ነው፡፡ እርግጥ በድርጅቱ ውስጥ አይቀሬ የሆኑት የአቋም፣ የጥቅምና የስልጣን ሽኩቻዎች ገና ክርረው ባልተከሰቱበት ሁኔታ የዚህ ድርጅት መሪዎች ዲሞክራሲ፣ ድምጽ ብልጫ፣ የሕግ የበላይነት፣ የጋራ አመራር (ኮሌክቲቭ ሊደርሺፕ) እያሉ ራሳቸውን ሊያታልሉ ይችላሉ፡፡ ልዩነቶች እየተካረሩ በሄዱ ቁጥር ግን ድርጅታቸው ከመሰረቱ አፋኝና ፀረ ዲሞክራቲክ ስለሆነ ያው እንደአብዮት የራሱን ልጆች መብላት ይጀምራል፡፡ ከዚህ አንጻር ሳየው እነ አቶ ስዬ ዛሬ ቴሌቪዥንን ተከለከልን፣ ሃሳባችንን መግለጽ አልቻልንም፣ መብታችንን ተገፈፍናል፣ የሕግ የበላይነት ተጥሷል ወዘተ ሲሉ «ባገር ከመጣ» አስር አመት የሆነውን ችግር ገና ዛሬ በነሱ ላይ ብቻ የወረደ አፈና አድርገው ቆጥረውታል ማለት ነው፡፡ የአድማስ ጥበት የምለው እዚህ ላይ ነው፡፡

ሁለተኛው ከዚህ ከዲሞክራሲ ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እነ አቶ መለስ በ«ቡርዥዋ ዲሞክራትነት» ተወንጅለዋል፡፡ ወዴት ከፍ ከፍ? እንደተባለው መሆኑ ነው፡፡ እኔ ይኸንን «ውንጀላ» ብዬ አልጠራውም፡፡ እነ አቶ ስዬ የቤተ-መንግስቱን አንጃ እያቀላመጡ ነው ያሉት፡፡ ለማንኛውም እነሱ ደግሞ ከቡርዥዋ ዲሞክራሲ ይልቅ ለገበሬውና ለወዝአደሩ የሚሆን ዲሞክራሲ እንቆማለን ባይ ናቸው፡፡ ወገናዊነት ከፋት የለውም፡፡ መኢሶንም ወገናዊ ነኝ ይላል፡፡ እንዲያውም የሁሉም ነኝ፣ ለሁሉም ነኝ የሚል፡፡ አልወገንም የሚል ድርጅት ካለ ይህ ድርጅት ዋሾ ድርጅት ነው፡፡ ጥያቄው ይህንን ወገናዊነት የምናራምደው እንዴት ነው? የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ነው፡፡ መኢሶን ከራሱም፣ ከሃገሪቱም፣ ከዓለምም ታሪክ ተምሯል፡፡ ዲሞክራሲ ለወገንኩት መደብ፣ ለወገንኩት ብሄር፣ ለወገንኩት ድርጅት ከተባለ ሌላው ቀርቶ ተወገነለተባለው ስብስብ ለራሱ አደገኛ ነው የሚል ትምህርት ቀስመናል፡፡ ሰዎቹ ራዕያቸውን ከእኛም ከዓለም አቀፉም ልምድ ቀስመው አላስፉትም የምለው እዚህ ላይ ነው፡፡ ሌላ ያልተገነዘቡት ጉዳይ እነሱ አስር አመት በገነቡት ስርዓት ቡርዥዋ ይሁን ሌላ በምንም ዓይነት ቅጽል የሚጠራ ዲሞክራሲ የለም፡፡ ዛሬ በሃገራችን የተተከለው የለየለት ፀረ ሕዝብ፣ ፀረ ዲሞክራሲ አፋኝ አገዛዝ ነው፡፡ የግድ እንዲህ አይነቱ ዲሞክራሲ ተብዬ ነገር ላይ የሆነ ቅጽል እንጨምርበት ከተባለ እኔ የቡርዥዋም የምንም አልለውም፡፡ የወሮበሎች ዲሞክራሲ ነው፡፡

ሌላው የብሄራዊ ነፃነትና የአገር ሉአላዊነት ነገር አንስተዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ➔

> ባለፈው ቃለ ምልልስ የወጣቱ ንቅናቄ ከአምቦ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ዘልቆ አዲስ አበባ መድረስ አቅቶታል እያልኩ ሳማርር የነበርኩ ሰው ዛሬ በማየው ደግሞ እጅግ ብኩራና ደስ ቢለኝ አያስገርምም፤
> ከተከፈለው መስዋዕትነት ባሻገር የዚህ ንቅናቄ ዋና ትርጉም ይህ ወጣቶቻችን ያሳዩት የአንድነትና የመተጋገዝ መንፈስ ነው

እንዳጋጣሚ ባለቤት ያጣ የትግል መስክ ብዬ ባለፈው ቃለ ምልልስ በሰፊው ለማብራራት ሞክሬያለሁ:: በአስር አመት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ድርጅት ወይም የድርጅት አንጃ ከሌላ ድርጅት ወይም አንጃ ጋር በዚህ ጥያቄ ላይ ልዩነት አለኝ ብሎ የብሔራዊ ነጻነትን ጉዳይ ሲያነሳ እኛም ደረት የምንመታበት እነሱም አይናችሁን ላፈር የሚባሉበት ምንም ምክንያት የለም:: በዚህ ጉዳይ ከአንዳንድ አካባቢዎች «ሰዎቹ የተለወጠው የዓለም ሁኔታ አልገባቸውም፤ ሰዎች እዛው ደደቢት ላይ ነው የቆሙት» የሚል አነጋገር ሲሰነዘር እጅግ ተገርሜያለሁ:: እኔ ደደቢትን ረግጬ አላውቅም:: ላለፉት ሰላሳ አምስት አመታት እዚሁ «ሲስተሙ» ውስጥ ነው የምኖረው፤ ለውጦችን እከታተላለሁ:: በዓለም ዙሪያ የሚካሄዱትን ትግሎች እከታተላለሁ:: አለም ተለዋውጣለች:: ዛሬ ሌላው ቀርቶ በተባበሩት መንግስታት ተቋሞችም ሆነ በሌሎች የሚታመነው ነገር ዓለም ይበልጥ ተዛብታለች የሚለው ሀቅ ነው:: ያለንበት ሁኔታ፣ የገባንበት ወይም እየገባንበት ያለነው አለም ጠንቅቆ ገብቶኛል ብዬ ባለፈው ቃለ ምልልስ ላይ በዓለም ታሪክ እንደ ጋራ የአገሮች ሕልውና፣ ብልፅግናና ማሕበራዊ ፍትሕ ከብሔራዊ ነፃነት ጥያቄ ጋር የተያያዘበት ወቅት የለም:: ባጭሩ እነ አቶ ስዬን የዓለም አቀፉ ሁኔታ አልገባቸውም የሚሉት ምሁራን ያልገባቸው እነሱ ራሳቸው ናቸው የሚል እምነት አለኝ::

እነዚህ ሰዎች ዛሬ አለም ተለውጣለች ብለው መቆም አይችሉም:: ዓለም ይበልጥ ተዛብታለች:: ከአገር የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ አንድ ሳይቀር ኢትዮጵያን እንዴት አገኛችኋት ብዬ ስጠይቃቸው ሁሉም የሚያወሩት ስለሕዝባችን መደህየትና ቀጠል አርገው ደግሞ ስለጥቂቶች ሰማይ የነካ ሃብት ማካበት ነው:: ይሄ በአገር የመጣ ብቻ አይደለም፤ በአለም የመጣ ክስተት ነው:: ይህንን ቃለ ምልልስ በማዘጋጅበት ሳምንት እነ ኮፊ አናን የተገኙበት ሶስተኛው ሊስት ዲቨሎፕድ (በማደግ ላይ ያሉ አገሮች) አለም አቀፍ ጉባኤ በብራሰልስ እየተካሄደ ነው:: ሊስት ዲቨሎፕድ የሚለው ዲፕሎማቲክ ቋንቋ መሆኑ ነው:: መናጢ ድሃ አገሮች ብሎ «ሰው ላለማስቀየም»:: በቀን ከአንድ ዶላር ያነሰ ገቢ ያላቸው ለማለት ነው:- በነፍስ ወከፍ:: የዛሬ ሃያ አመት እንዲህ አይነቱ ጉባኤ ለውጥ የሚያመጣ መስሎኝ ፓሪስ ሲደረግ እኔም ተሳትፌያለሁ:: ያኔ እነዚህ መናጢ ድሃ አገሮች ሃያ አምስት ነበሩ:: ከነዚያ ውስጥ ከዚህ ረድፍ የወጣችው ባላት የአልማዝ ክምችት ቦትስዋና ብቻ ነች:: ዛሬ ሶስተኛው ጉባኤ ላይ ቁጥራቸው 49 ደርሷል:: ያውም እንግዲህ ተመድ የሚለው የድሆች አገሮች ቁጥር ጨምሯል ነው:: በነዚህ አገሮች ውስጥ የሚኖርት ሕዝቦች ያሉበት የማጣትና የመራቆት ደረጃ ከዛሬ ሃያ አመት ዛሬ ይበልጥ ከፍቷል:: ተመድ መናጢ ድህነትን በአስራ አምስት አመት ውስጥ በግማሽ ለመቀነስ እቅድ አውጥቶ ነበር:- በ2015 ዓ.ም ግድም:: ከአስር ቀን በፊት የፕሮግራሙ ኃላፊ ለቢቢሲ ኢንተርቪው ሲሰጡ ያስተላለፉት መልእክት «ነገሩ እንደታሰበው ቀላል አይሆንም» የሚል ነበር:: ይኸን ሁሉ የምለው ዛሬ በመተከል ላይ ያለውን አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርአት መጠየቅ ኋላ-ቀር፣ አክራሪ፣ ነገር ያልገባው አያሰኝም ለማለት ነው::

**ኢትኦጵ:- የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከዚያም ወደ መላ አገሪቱ ወጣቶች የተዛመተውን ንቅናቄ እንዴት ተመለከቱት?**

*ዶ/ር* ነገደ:- የተማሪዎቹ ንቅናቄ ተገቢ የመብት ጥያቄዎችን ያነሳ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ነው:: ከቁጥጥር ውጭ ወጥቶ ይህ ሁሉ ወጣት ቢሰዋና ንብረት ቢወድምም፣ ለዚህ ሙሉ በሙሉ ተጠያቂው የወያኔ መንግስት ነው:: ከተማ ውስጥ ሽብርና ዘረፋ ስለተስፋፋ ይህንን የግፍ እርምጃ ወሰድኩ የሚለው መንግስት የጸጥታ ኃይሎች ከዚህ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ መንገድና አደባባይ ላይ ሳይሆን ዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ መኝታ ቤት ድረስ እየገቡ ሲተኩሱ እነደነበሩ እንዴት ይረሳል?

ሕወሐት በራሱ የውስጥ መሰነጣጠቅ ውጥረት ውስጥ እያለ የእነሱን ሽኩቻና ግጭት ይበልጥ አጉልቶ በሚያሳይ መልክ የሃገራችን ወጣቶች የብሔርና የክልል አጥር ሳያግዳቸው ከመቀሌ እስከ አርባምንጭ፣ ከጅማ እስከ አለማያ በአንድነት እየተደጋገፉ ተነሱ:: ባለፈው ቃለ ምልልስ የወጣቱ ንቅናቄ ከአምቦ ሰላሳ ኪሎ ሜትር ዘልቆ አዲስ አበባ መድረስ አቅቶታል እያልኩ ሳማርር የነበርኩ ሰው ዛሬ በማየው ደግሞ እጅግ ብኩራና ደስ ቢለኝ አያስገርምም:: ከተከፈለው መስዋዕትነት ባሻገር የዚህ ንቅናቄ ዋና ትርጉም ይህ ወጣቶቻችን ያሳዩት የአንድነትና የመተጋገዝ መንፈስ ነው:: ወያኔዎችም እጅግ የተደናገጡት በዚህ ይመስለኛል:: ማንንም ሳይጠይቃቸው አልተዳከምንም እያሉ በመግለጫ እየወተወቱ የድክመት ምልክት በሆነው የጭፍጨፋ ጎዳና ተሰማሩ::

የተማሪዎቹም ሆነ በአጠቃላይ ለዴሞክራሲ የሚደረገው ትግል እንዴት ይቀጥል የሚለውን ጥያቄ ዝቅ ብዬ እመጣበታለሁ:: እዚህ ላይ ግን «ሂዩማን ራይትስ ዎች» የተባለው ድርጅት በትክክል እንዳስቀመጠው ወያኔዎች ሆን ብለው ችግሩ ከቁጥጥር ስር እንዳይውል፣ በዚህ ሰበብ ተጠቅመው ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎችንና የሲቪክ ድርጅቶችን እንደዚህም ነጻውን ፕሬስ ለማኮላሸት የተጠቀሙበትን ስትራቴጂ በደንብ መግለፅ የሚያስፈልግ ይመስለኛል::

የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ የተካሄደው አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ቀቢፀ ተስፋ የሆነና የወያኔ የኢኮኖሚ ስርአት ቀኑን አጨልሞበት የተቀጣና በልኩ ያመጸ ወጣት በሚኖርበት ከተማ ነው:: ከተማሪው ትግል ጋር ይህ እነሱ «ቦዘኔ» የሚሉት ክፍል ተደባልቋል፣ ሰብሯል፣ ዘርፏል:: እዚህ ላይ መቼስ የዳቦ ሌባ ጉዳይ ከተነሳ አይቀር በቀኝና በግራ ሃይሎች መካከል ስላለው ዘላለማዊ ሊባል ስለሚችለው የአይታ ልዩነት ሳያወሱ ማለፍ የሚቻል አይመስለኝም:: የቀኝ ኃይሎች ድሮውንም ሰው መጥፎ ነው ከሚለው መጥፎ አስተሳሰብ ስለሚነሱ ዳቦ ቢሰረቅ ጣታቸውን ወደሌላው ሌባ ነው የሚቀስሩት:: የግራ ኃይሎች ግን ሰው ንፁህና ክቡር ነው፤ ሌባ ወይም ቦዘኔ ይሆናል እንጂ ከእናቱ ማሕጸን ሌባ ወይም ቦዘኔ ሆኖ አይወለድም በሚል እይታ ስለሚነሱ ጣታቸውን የሚቀስሩት ዳቦ እንዲሰርቅ ያደረገው ስርዓት ላይ ነው:: እርግጥ የተፈጸመውን ዘረፋና ውንብድና ማውገዝ ያስፈልጋል:: እኛ ግን ከሁሉም በላይ የምንወነጅለውና ጣታችንን መቀሰር ያለብን ወጣቱን በጅምላ እንደዚህ ተስፋ ያስቆረጠውን፣ መፈናፈኛ ያሳጣውን እነ አቶ መለስ በተከሉት ስርዓት ላይ ነው::

ሁለተኛ ደግሞ የወያኔ መሪዎች ራሳቸው የፈለፈሉት፣ የነሱ የራሳቸው ቅስቀሳ ውጤት የሆነው፣ እነሱ ራሳቸው ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን ባደረጉት ሁኔታ ተጠቅመው፣ ራሳቸው «ተገቢ ጥያቄ ነው ያነሳው» ያሉትን የተማሪ እንቅስቃሴ ጥላሸት ከመቀባት አልፈው ተርፈው በዚህ ሰበብ ተቃዋሚዎችን ለመምታት ላይ ታች ሲሉ በኢትዮጵያ ሕዝብም ፊት ሆነ አቀፉ ደግፊው ባቀይዋቸው ባዕዳንም ፊት ሙሉ በሙሉ እንዲጋለጡ ማድረግ ያስፈልጋል:: ምዕራባውያን በሙሉ የተፈፀመውን ግድያ አውግዘዋል:: ይኸ ተገቢና በጎ ነገር ነው:: በሌላ በኩል ግን የወያኔን ክርክር ቀልበው «ነገሮች እንዲህ ከቁጥጥር ውጭ ሲሆኑና ዝርፊያና ውንብድና ሲስፋፋ መንግስት ፀጥታ የማስከበር ሃላፊነት አለበት» የሚለውንም ነጥብ አያስመሩበት ሁሉም እንደ አንድ ሰው የተቀባበሏትና በየመግለጫው ይፋ ያደረጓት ወያኔን ኤክስሲቭ ፎርስ ተጠቀመ ብላ የምትገስፅ ቃል ነች:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ በዚያው ሳምንት በካናዳ ከ48 ሰአት በላይ የቆየ ፀረ ግሎባላይዜሽን አመጽ ተካሄዷል:: ብዙ ንብረትም ወድሟል:: ጥቂት ወጣቶች ቢቆስሉም አንድም ሰው አልሞተም:: ፖሊስ የወጣቱን አመጽ ለመቋቋምና ለመቆጣጠር የሞከረው በውሃና በአስለቃሽ ጋዝ እየተጠቀመ ነበር:: በኛ አገር ለምን እንዲህ አልተደረገም? ነገሩ እንደዚህ ሆኖ ሳለ በኛ አገር «ቦዘኔ» በተባለውም ሆነ በሌሎች ዜጎች ላይ የዘነበው ውሃ ሳይሆን ጥይት ሆኖ ሳለ ኤክሰሲቭ ፎርስ ብሎ መሸኘት የሚቻል አይመስለኝም::

**ኢትኦጵ:-ይህ የተወሰደው የኃይል እርምጃ ለችግሩ መፍትሄ ይሆናል ብለው ያስባሉ? በዚህ ዙሪያ በአጠቃላይ የሚሰጡን አስተያየት ካለ?**

*(ከዶ/ር ነገደ ጎበዜ ጋር የተደረገው ቃል ምልልስ አላበቃም፤ ከላይ የሰፈረውን ጥያቄ ጨምሮ... የአገዛዙ የመጨረሻ አማራጮች ምንድን ናቸው? የሚፈጠረውን ክፍተት ማን ይሞላል? ለሚሉትና ለመሳሰሉት ወቅታዊ ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽ በዶ/ር ነገደ ፈቃድ የፊታችን ረቡዕ በሚታተመው ግንቦት 22/1993 ዓ.ም ኢትኦጵ ጋዜጣ ይቀጥላል)*